# እንግዶች እንኳን ደህና መጣችሁ!

**በቤተ ክርቲያን የተዘጋጀ ታላቅ ሪትሪት**

አንዳንድ ማሳሰቢያዎች:

- ከችካጎ የምንለቀው July 4 at 10 a.m. ይሆናል።
- ቦታው በ 1p.m. ለመድረስ እናስብለን።
- አድራሻ: W2511 WI-23, Green Lake, WI 54941
- ሁላችንም በየራሳችን መኪና እንመጣለን።
- ትራንስፓርት የምትፈልጉ አስታውቁን።
- መጫወቻወች እንደ ኳስ የመሳሰሉ ይዛችሁ ለመምጣት የምትችሉ ለእህት ዲቦራ አስታውቁ።

**የአርብ ፕሮግራም**

በአርብ ፕሮግራም እግዚአብሔር ግሩም የጸሎትና የትምህርት ጊዜ እየሰጠን ነው። በዚህ የጸሎት ፕሮግራም ላይ በመገኘት በጸሎትና ቃሉን በመማር እንድንተጋ ቤተ ክርስቲያን ታሳስባለች። እንዲጸለይላችሁ የምትፈልጉ ወገኖችም መሪዎችን ማነጋገር ትችላላችሁ። ጌታ ይባርካችሁ።

"ወደ ውጭም አውጥቶ፦ ጌቶች ሆይ፥ እድን ዘንድ ምን ማድረግ ይገባኛል? አላቸው።
እነርሱም፦ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እመን አንተና ቤተ ሰዎችህ ትድናላችሁ አሉት።" (ሐዋ. 16፡ 30-31)



⇒ **የእሁድ ፕሮግራም ይካፈላሉ?**
⇒ **የአርብ ፕሮግራም ይካፈላሉ?**
⇒ **በምጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ይካፈላሉ?**
⇒ **ማገልገል ይፈልጋሉ?**
⇒ **Yeec.org App ጭነዋል?**
⇒ **http://www.yeec.org/ ይጎበኛሉ?**

**ሽማግሌዎችን ለማግኘት፦**

773-886-0818 (ወ/ም ሲሳይ)
773-507-0147 (ወ/ም ጸደቀ)
630-677-0293 (ዶ/ር ተረፈ)
773-910-0486 (እ/ት ሰናይት)
773-556-5345 (ወ/ም ረድኤቱ)

**<u>መደበኛ ፕሮግራሞች</u>**

እሑድ 1:30 p.m. -- 4:30 p.m.
አርብ 7:00 p.m. -- 9:00 p.m.

| የችካጎ የምስራች ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን | | Chicago Yemsrach Evangelical Church |
|---|---|---|

"እነሆ፥ ለሕዝቡ ሁሉ የሚሆን ታላቅ ደስታ የምሥራች እነግራችኋለሁና አትፍሩ" ሉቃስ 2:10



"እግዚአብሔርም ስለ ምድሩ ቀና፥ ለሕዝቡም ራራለት።"
(ኢዮኤል 2:18)

Chicago Yemsrach Evangelical Church
4455 N. Seeley Avenue
Chicago, IL 60625

መደበኛ ፕሮግራሞች

እሑድ 1:30 p.m. -- 4:30 p.m.

**June 30, 2019**

**ሰኔ 23፣ 2011 ዓ.ም.**

## የእለቱ አገልግሎት መርሃ-ግብር

| | |
|---|---|
| ጸሎት ................. | እህት ሒሩት ተስፉ |
| አምልኮ....................... | የቤተ ክርስቲያን የአምልኮ ቡድን |
| ፕሮግራም መሪ .......... | ወንድም ረድኤቱ ግርማ ካሳ |
| ቃል ............. | ወ/ም ዘሪሁን ዳዊት |
| ማጠቃለያ ................. | ፕሮግራም መሪ |

## <u>የሳምንቱ ጥቅስ</u>

የእግዚአብሔርም አገልጋዮች ካህናት ከወለሉና ከመሠዊያው መካከል እያለቀሱ፡- አቤቱ፥ ለሕዝብህ ራራ፥ አሕዛብም እንዳይነቅፉአቸው ርስትህን ለማላገጫ አሳልፈህ አትስጥ፤ ከአሕዛብ መካከል፡- አምላካቸው ወዴት ነው? ስለ ምን ይላሉ? ይበሉ።

እግዚአብሔርም ስለ ምድሩ ቀና፥ ለሕዝቡም ራራለት። (ኢዮኤል 2፤17-18)

**የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድኖች**

| መሪ | ቀን | አድራሻ |
|---|---|---|
| ወ/ም አያሌው አስፋው | ማክሰኞ | 5030 N. Marine Dr., Chicago, IL 60640 |
| እህት ሰናይት ከበደ | ማክሰኞ | 7200 N. Ridge Ave., Chicago IL 60660 |
| ዶ/ር ተረፈ አንሼቦ | ማክሰኞ | 7526 N. Ridge Blvd., Unit #3W, Chicago IL 60645 |
| ወ/ም ረድኤቱ ካሳ | ሃሙስ | 7252 W. Everell Ave., Chicago, IL 60631 |
| ወ/ም ሳሚ ኃብተየስ | ሰኞ | 9107 Laramie St. Skokie, IL 60077 |
| ወ/ም ዮናስ ባህሩ | ማክሰኞ | 5523 N. Kenmore Ave., Chicago, IL 60640 |
| | | |

## መልዕክተ ሰንበት

ወ/ም ረድኤቱ ካሳ

### በስሜ የተጠሩት ሕዝቤ።

*"በስሜ የተጠሩት ሕዝቤ ሰውነታቸውን አዋርደው ቢጸልዩ፥ ፊቴንም ቢፈልጉ፥ ከክፉ መንገዳቸውም ቢመለሱ፥ በሰማይ ሆኜ እሰማለሁ፥ ኃጢአታቸውንም ይቅር እላለሁ፥ ምድራቸውንም እፈውሳለሁ።" (2 ዜና 7:14)*

ክርስቲያኖች ካሉን ተስፋዎች መካከል በከፍተኛ ስፍራ የምናስቀምጠው አንዱ አምላካችን እግዚአብሔር ጸሎትን ሰምቶ የሚመልስ መሆኑ ነው። በዚህ ስፍራ እንደምናነበው እግዚአብሔር በስሙ ለተጠሩት ሕዝቡ የገባው ተስፋ አለ። ተስፋው ግን ቅድመ ሁኔታዎች አሉት። የመጀመሪያው በእግዚአብሔር ፊት ትሁት መሆን ነው። ሁለተኛው የእግዚአብሔር ፊት በጸሎት መፈለግ ነው። ሶስተኛው ከክፉ መንገድ መመለስ ነው። ይህ ሲሆን እግዚአብሔር ይሰማናል፣ ይቅር ይለናል፣ ደግሞም ይፈውሰናል።

ለሚገጥሙን ማንኛውም ግላዊና አገራዊ ጉዳዮች ትልቁ መፍትሔ በእግዚአብሔር ፊት በትህትና መጸለይ ነው። በአውዱ ላይ እደምንመለከተው ይህ ትልቅ የጸሎት መልስ ተስፋ የተሰጠው አገራዊ በሆነ ጉዳይ ላይ ነው። እግዚአብሔር ህዝቡን ለመቅጣት ዝናብን ቢከለክል፣ ምድሪቱን ይበላ ዘንድ አንበጣን ቢያዝ ወይንም ቸነፈርን ቢያዝዝ ለዚህ አገራዊ ችግር መፍትሔ ያለው በስሙ በተጠሩት ህዝቡ ዘንድ ነው። አሳሳቢ ሁኔታዎች ሲገጥሙ በትህትና በታላቁ ጌታ ፊት በጸሎት መውደቅ ወሳኝ ነው። በተለይም ቤተ ክርስቲያን ዋናው ማድረግ ያለባት ይህ መሆን አለበት። የራሳችንን ማስተዋል ተጠቅመን ችግሩን ለመፍታት ከመጣር ይልቅ አስቀድመን እግዚአብሔር ሆይ አባክህን ይህንን ጉዳይ ተመልከተው ብለን በጸሎት ብንቀርብ መልስ ከሰማይ ይመጣልናል።

የእግዚአብሔርን ፊት መፈለግ ወደ እርሱ በምልጃ መሮጥ ነው። እርሱን የሙጥኝ ማለት ነው። ሰው በመከራው ጊዜ የበለጠ የእግዚአብሔርን ፊት መፈለግ አለበት። የአገር ሸክም የከበዳቸው አባቶች ያደርጉ የነበረው የሕዛባቸውን መተላለፍ ይዘው ፊቱን መፈለግ ነው። ነህምያ የኢየሩሳሌምን መፍረስና መቃጠል ሲሰማ ለአያሌ ቀናት በጾምና በጸሎት በንስሃም የእግዚአብሔርን ፊት ፈለገ። በእግዚብሔር ፊት እንደ መሪ የሕቡን መተላለፍ ይዞ ቀረበ። አለቀሰ። ነስሃ ገባ። ነህምያ መፍትሔ ፍለጋ ያገለግለው ወደ ነበረው ንጉስ አልገባም። ወይንም አስቀድሞ ችግሩን ለመፍታት አልተንቀሳቀሰም። ነገር ግን አስቀድም የአምላኩን ፊት በጽኑ ፈለገ። ቃል-ኪዳኑን አስታወሰ። ምሕረትና ሞገስን ጠየቀ። እግዚአብሔርም ዘምበል አለለት። ዳንኤልም የኢየሩሳሌም የሰባ አመት ምርኮ የሚፈጸምበትን ከመጽሐፍ ሲረዳ ያደረገው አንድ ነገር በንስሃ የአምላኩን ፊት መፈለግ ነበር። እግዝዚአብሔርም በፊቱ የጸለዩትን የንስሃ ጸሎት ሰምቶ አሰባቸው። ከውድቀትም አዳናቸው።

ወገኖቼ፡- ለችግራችን መፍተሔ ያለው በእግዚአብሔር እጅ ነው። አይኖቻችንን ወደ ተራሮች ብናነሳ እርዳታ አናገኝም። እርዳታችን ያለው ከሰማይ አምላክ ዘንድ ነው። ለምንኖርባት ከተማ ችግርም ሆነ ለተወለድንባት አገር ችግር እግዚአብሔር ምህርትን የሚያደርገው በሰሙ የተጠራነው ህዝቡ እራሳችንን አዋርደን እንደ ነህምያ በጸሎትና በንስሃ በፊቱ ስንቀርብ ነው። ያን ጊዜ የሰማይ አምላክ ይሰማናል። ይቅር የለናል። ስብራታችንንም ይጠግናል። አሜን!